በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

/የተዋሕዶ መዝሙር - በመዘምራን ከውስጥ ይደመጣል፡፡ ተዋሕዶን የምትወክል ሴት ረዘም ያለ ቀሚስ፣ ካባ ደርባ አክሊል ደፍታ ትቆማለች፡፡ በዙሪያዋ ባህታዊ፣ ወጣት፣ ሕፃን ቆመዋል፡፡ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ፣ ቅዱስ ባስሊዮስ፣ አባ ጊዮርጊስ ከበስተጎላዋ አሉ፡፡/

<u>ተዋሕዶ፦</u> **አዎ እኔ ነኝ**
እኔ ነኝ ተዋሕዶ . . .
ያነጻኝ በደሙ
ያስጠራኝ በስሙ፤
ያቆመኝ በዓለት
ፍጹም አልናወጽ - እውነተኛ ፍኖት፤
ከሰማዩ ሀገር
መሠረት ያረገኝ ያወጀኝ በፍቅር፤
እኔን ተዋሕዶ
ለቀረበኝ ወዶ፤
ለተጓዘ ታምኖ
ለመጣ ወስኖ፤
አክሊል እንዲቀዳጅ
ከአምላክ አንዲወዳጅ፤
እውነትን - ፍቅርን - ተስፋን የምሰንቅ
ለክብር የማመጥቅ፤
ያኔ በሰማያት በመላእክት ሕብረት
የነበርኩ በምሥጢር እውነተኛ እምነት፤
በዘመነ አበው ከልብ ከትሜ
በዘመነ ብሉይ በሕግ ታትሜ፤
ለአዳምና ልጁ ፍኖት የነበርኩኝ
በዘመነ ሐዲስ በገሀድ ወጥቼ
በደሙ ታንጬ፤
አበው ሐዋርያት
ሊቃውንት ሰማዕታት፤
ስለ አምላክ መስክረው እውትን ተናግረው
ክብር ያገኙብኝ ዓለምን ድል አርገው፤
እኔ ነኝ ተዋሕዶ
ያነጻኝ በደሙ
እውነተኛ ፍኖት የጠራኝ በስሙ፡፡
ሥርዓት ትውፊቴ
ቀኖናና ሕጌ ...
ንጹሕ የተጣራ ከቶም የማይሻር
ለትውልድ ትውልድ የሚደርስ ለልጅ ልጅ
የማላረጅ የማላፈጅ
ከክህደት የማልወዳጅ፤
ነፍሱን ብሎ ለመረጠኝ
ክብሩን ጥሎ ላከበረኝ፤
የክብር ዘውድ ይደፋ ዘንድ
ምሆንለት ቀና መንገድ፤

ዘመን አልፎ ዘመነ ቢተካ ዘመን ቢመጣ
የማልወይብ የማልነጣ፤
እኔ ነኝ ተዋሕዶ
ያነጻኝ በደሙ
እውነተኛ ፍኖት የጠራኝ በስሙ፡፡
/መዝሙር - ቅድስት ተዋሕዶ ንጽሕት እምነት .../
/ወደ ከበቧት ልጆች እየተመለከተች .../
ተነሡ ልጆቼ ስለ እኔ መስክሩ
እውነተኛ መንገድ መሆኔን ንገሩ፡፡
የሰናፍጭ ቅንጣት ጉድፍ እንደሌለኝ
ኑ ! ኑ ! ልጆቼ ኑ እስኪ ! መስክሩልኝ !
አለ ዲዮስቆሮስ . . .
የሚናገርልኝ ለእኔ ተዋሕዶ
በእኔ ፍቅር ለቡ ነዶ፤
በአላውያን ነገሥታት
በውልደ ክህደት፤
መሐል ተሰይሞ
መከራ ጫፍ ቆሞ፤
ጥርሶቹ ረግፈው - ዕዕሙ ተነጭቶ
ብዙ ተንከራቶ፤
እውነትን ጨብጦ፤
ሐሰትን ርቆ
የዘዓለም ክብርን በልቡ ሰንቆ፤
የመሰከረ ለአምላኩ
አለ ዲዮስቆሮስ ...
<u>ዲዮስቆሮስ፡-</u> ክብር ያገኘሁብሽ . . .
ዛሬ ዘመን ረቆ
ሥልጣኔ ዘልቆ፤
የእምነት መነጽሩን ከዓይኑ አውልቆ፤
ካላየሁ ካልዳሰስኩ
ሁሉን ካልመረመርኩ፤
አላምን አልሄድም በተዋሕዶ ፍኖት
ብሎ ትውልድ ቢል ተይዞ በክህደት፤
ክብሩን ያጣል እንጂ አንቺ ምን ጐድሎብሽ
ጽኑ መሠረትሽ፤
የቀና ፍኖትሽ፤
ያተመሽ - ያጸናሽ - በፍቅር በደሙ
ያወደሽ ሰላሙ፤
የጠራሽ በስሙ፤
እርሱ ነው ፈጣሪሽ
ፍጹም ላትፈርሺ በዓለት ያጸናሽ፡፡
አድምጠኝ ወገኔ
የእምዬ ልጅ ስማኝ . . .
የአንተን የህልም ቅዠት
ፍሬ አልባን ክህደት፤
ቀድሞ የነበሩ የሐሰት ወዳጆች
አልመውት ነበር ርቀው ከእውነት፡፡

ዛሬ በዚህ ዘመን አዲስ ክህደት የለም
የአርዮስ - ንስጥሮስ - ፍጢሞስ - ስበልዮስ
የእነርሱን ቅዠት ነው አሁን የምታልም፡፡
ወደቁበት እንጂ
መች ክብርን ለበሱ
ተኮነኑ እንጂ መቼ ተወደሱ፤
በጥርጥር ማዕበል
ሕይወታቸው ነፍዞ
ሕሊናቸው ናውዞ፤
ከንቱ እንዳሰቡ - ከንቱ እንደያዙ
መቃብር ተጓዙ፡፡
(ወደ ተዋሕዶ እየጠቆመ . . .)
እሷ ናት ተዋሕዶ
የከበባት እውነት
መድኅን ያተማት፤
የዋጃት በደሙ
የጠራት በስሙ፤
አጥብቀህ እርሷን ያዝ
በጥርጥር አትናውዝ !!
ብዙ መርምሯል
ብዙ ተምሯል
ምሥጢርን አራቆ መጽሐፍን ጽፏል፡፡
አድምጠው ወገኔ . . .
ስለ ተዋሕዶ - እርሱ ይንገራችሁ
ክብሯን ያስረዳችሁ፤
ሥጋውን ጐስሞ
ነፍሱን አስቀድሞ፤
ለሃይማኖት ታግሎ
ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ጊዮርጊስ ይባላል፡፡
(ቀስ አያለ ይገባል ቅድስት ተዋሕዶ ይዘመራል)...
<u>አባ ጊዮርጊስ</u>፦ ሥርዓቷ ንጹህ ቀኖናዋ ቅዱስ
አምሳል የምትሆን ለሰማዩ መቅደስ፤
ዘመን የማያስረጃት
ወረት የማይለውጣት፤
በእምነት መነጽር አስተውሎ ላያት
እውነት የሞላባት፤
በዓለም እይታ የመሰለች ተራ
ግን የሆነች አውራ፤
መቼም የማትፈርስ
መቼም የማትታደስ፤
እርሷ ናት ተዋሕዶ እውነተኛ ፍኖት፡፡
ኢየሱስ ክርስቶስ ያተማት በደሙ
ያወዳት ሰላሙ ፤
ያስጠራት በስሙ፤
ዝማሬው ቅዳሴው
ሰዓታት ውዳሴው፤

ጾም ጸሎት ስግደቱ
ትሩፋት ምጽዋቱ፤
የሐዘን የደስታ - መግለጫ ሥርዓቱ
በዓላት ትምህርቱ፤
እንዳይመስልህ ተራ ዘመን የሚሸረው
ጊዜ የሚለውጠው
የሰማይ ሥርዓት ነው፤
የታዘዘ ከአምላክ
ክብርን የሚያላብስ - እንደሰማይ መልአክ፤
መተግበር ቢከብድህ - ቢሳንህ መፈጸም
ብትማርክህ ዓለም፤
የአባቶችህን ገድል
ይሻሻል ይቀየር - ለማለት ታጥቀሃል።
ድንበር ላፍርስ አልክ
በስንፍና ወደቅክ፤
ይልቅስ አድሰው - የአንተን ልቦና
እንዲያስብ ቀና።
ወኔን እንዲላበስ - የአበው ሊቃውንቱን
የሰማዕታቱን፤
እነርሱ እንደጸኑ - አንተም ጽና ይልቅ
በክብር እንድትደምቅ።
ተዋሕዶ እንደው - ዶግማዋ አይሻርም
የአምልኮ ሥርዓቷም - ከቶ አይለወጥም።
አታረጅም እርሷ
ሁሌ አዲስ ናት እርሷ።
ቀና ነው ፍኖቷ
በእምነት ለኖረ ሰው
ትላንት ለነበረው
ዛሬም ለሚኖረው
ነገም ለሚመጣው
ፍጹም የተመቸ - ቀና ነው ሥርዓቷ፤
እውነት ነው ፍኖቷ።
ይልቅ አንተው ታደስ - ከጥርጥር ውጣ
የአርዮስ ንስጥሮስ - እንዳይሆን ያንተ ዕጣ።
(ቀስ እያለ ይገባል . . .)
ለቅድስት ተዋሕዶ - ንጽሕት እምነት
አርአያዋን አድምጥ - የቅድስት አርሴማን - ጽኑ ሰማዕት፤
ለአምላክ ሙሽራ - ብታደርግ ራሷን
ሥጋዋን ስትጐስም - አስበልጣ ነፍሷን፤
እጅ አልሰጥም ብላ - ለጣዖት አምልኮ
በፈጣሪዋ ፍቅር - ልቧ ተማርኮ፤
ፍጹም ሳያሳሳት - ውበት ደምግባቷ
ጸንታ በሃይማኖቷ፤
ለተዋሕዶ እምነት የመሰከረችን
ደጓ ሰማዕቷን - አድምጧት አርሴማን።
እጅግ ከተዋበ - ከቤተመንግሥቱ
ከተንቆጠቆጠ በእንቁና በወርቅ - ከዓለም ማንነቱ፤

ጾም ጸሎትን መርጣ
ሰማዕት የሆነች - ነፍሷን አስበልጣ፤
ቅድስቲቷን አናት
አርሴማን አድምጧት፡፡

ቅድስት አርሴማ፦ ዓለማዊ ኑሮ - ሁሉም ነገር ያልፋል
ከጊዜ ጋር አብሮ - ታሪክም ይረሳል፡፡
ልብህ አይንበርከክ - በጊዜያዊ ጥቅም
ቅርብ ትቀራለህ - አርቀህ ስታልም፡፡
ገንዘብም ይጠፋል
ንብረትም ይወድማል፤
ውበት ደምግባትም - ይቀራል ይከስማል፡፡
ለጊዜ አስደስቶ
ሰላም ፍቅር ነስቶ፤
ሁሉም ነገር ያልፋል
በምድር ይቀራል፡፡
ለጊዜያዊ ጥቅም
አትደለል ፍጹም፡፡
እምነትህን ጠብቅ
በክብር እንድትደምቅ፡፡
ጥቂት ለግሰውህ - ያለህን ሊያሳጡ
ክህደትን ሰንቀው - ወደአንተ ሲመጡ፤
አልሻም በላቸው - ከተዋሕዶ ሌላ
እርሷ ናት ሰላምህ - የሕይወትህ ተድላ፡፡
እርሷ ናት ውበትህ
ጌጥህ ሽልማትህ፤
የዘለዓለም ክብርን የምታላብስህ፡፡
ተዋሕዶ እናትህን - ውደዳት ከልብህ
ሥርዓቷን ጠብቅ
ትውፊቷን ተረከብ
በሕሊናህ ሳለው - አስቀምጥ ከልብህ፡፡
ከጊዜው ጋር አብሮ
መልኩንም ቀይሮ፤
ሲመጣ ክህደት
ንቃ እውቀበት፤
አልፈልግም በለው - ከተዋሕዶ ሌላ
እርሷ ናት ሰላምህ - የአንተነትህ ተድላ፡፡
እየሞትክ ሕይወትን የምትለብስባት
የክብርን አክሊል የምትቀዳጅባት፡፡
ቅድስት ተዋሕዶ . . . ቅድስት ተዋህዶ . . .

/ተዋሕዶ በኩራት ሆና አንገቷን ቀና አድርጋ በደስታ መንፈስ ወደ አረጋዊው - ወጣት - ህፃን እያየች . . ./

ተዋሕዶ፦ አያችሁ ልጆቼ
የዓይኔ ስስቶቼ፤
ያኔ አባቶቻችሁ - እውነትን ጨብጠው
እውነትን ተጫምተው፤

እውነትን መስክረው
ለሰይፍ ለእሳት - ሥጋቸውን ሰጥተው፤
ነፍሳቸውን መርጠው
ከአንበሳ ጋር ታግለው፤
ከእሳት ተጥለው
ክብርን ተሸልመው፤
ለዓለም ሙት ሆነው
ይሉኝታን ሳይዙ - እምነትን ጨብጠው፤
እስከዛሬ ያቆዩኝ እንደዚህ ሆነው ነው።

/በተሰበረ መንፈስ . . ./

ዛሬ ግን ተወልዶ
በጉያዬ ታቅፎ፤
ከእጄ እንጀራን ጐርሶ
በጀርባዬ ታዝሎ፤
እንዳላደገብኝ . . .
እንዳልተማረብኝ፤
እውነቱ ከልቡ - ከሕሊናው ሳለ
በይሉኝታ ገመድ - አፉ ተሸበበ።
የማስመሰል ኑሮን - ገንዘብ አደረገ
ሥጋዊውን ጥቅም - ደፍሮ አደገደገ።
ከአርዮስ ውላጆች - ከጠላቱ አበረ
በአባቶቹ ገድል - እርሱ አንዳልከበረ።
ለትውልድ ታሪክን - ትውፊት ሥርዓትን
ዘነጋው ማውረሱን፤
በቅሎ ልሁን አለ ለራሱ አሰበ
በአባቶቹ ገድል ወይ አልተወደሰ - ለሚመጣው ትውልድ ፍጹም አላሰበ።
ላድስልሽ አለኝ - ቀናው ሥርዓቴን
በጐ አምልኮቴን፤
ከተራ ቆጠረው - በዓለት መታነጼን።
ታዲያ ማነው ዛሬ
የሚጸና ከሥሬ፤
የአባቶቹን ፍኖት ማነው የመረጠ
ለክብር የቋመጠ።

<u>አረጋዊው - ወጣቱ - ሕፃኑ</u> . . .

እኛ አለን ተወሕዶ
ማን ተጐዳ አንቺን ወዶ፤
በፍኖት እንሄዳለን
ሥርዓትሽን እንጠብቃን።
በዓለት ላይ መጽናትሽን
የሰማይ መቅደስ - አምሳል መሆንሽን
ዘመን ጊዜ የማይለውጥሽ መሆንሽን፤
እንነግራለን ለትውልዱ
እንዳይወጣ ከመንገዱ፤
ሰርጐ ገቡን ልንመነጥር
ሥርዓትሽን ልናስከብር፤
ቃል ገባን ተዋሕዶ - ቃል ገባን እናታችን
ሳናስደፍር አንቺነትሽን።

/ከእግሯ ሥር ሄደው በርከክ ይላሉ በእጆቿ እራሳቸውን እየዳበሰች .../

ተዋሕዶ፦ ይደክማል እንጂ በከንቱ
አይለወጥ ሥርዓቱ።
ያጸናኝ አርሱ እግዚአብሔር
ሰማያዊ የሆንኩ ሳለሁ ምድር፤
እኔ ነኝ . . . እኔ ነኝ ተዋሕዶ . . .
እውነተኛ ፍኖት ያነጸኝ በደሙ
ያወደኝ ሰላሙ፤
ያስጠራኝ በስሙ፤
ዘለዓለም የምኖር ከቶ የማልናወጥ
መቼም የማልለወጥ።

/ ሁሉም የተዋህዶ መዝሙር እየዘመሩ ይወጣሉ። /

ተፈጸመ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር
አሜን።

ተዋንያን፦ 1. ተዋህዶ -
2. ዲዮስቆሮስ -
3. አባ ጊዮርጊስ -
4. አርሴማ -
5. አረጋዊ -
6. ወጣት -
7. ህፃን -
8. መዘምራን -